የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳
አዲስ አበባ ጥር ፰ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

24th Year No.20
ADDIS ABABA, 16th January , 2018

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፱/፪ሺ፲ ዓ.ም

ለአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጂት ቦታ ማዛወሪያ እና ማዘመኛ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከፈረንሳይ የልማት ድርጅት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ………………ገፅ ፩ሺ፷፮

**CONTENT**

Proclamation No.1069/2018

French Development Agency Credit Facility Agreement for Financing the Relocation and Modernization of the Addis Ababa Abattoris Enterprise Project Ratification Proclamation …………..page 1066

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፱/፪ሺ፲

## በኢትዮድያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ድርጅት መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለአዲስ አበባ ቄራዎች የድርጅት ቦታ ማዛወሪያ እና ማዘመኛ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፸ ሚሊዮን ዩሮ (ሰባ ሚሊዮን ዩሮ) ብድር የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮድያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ የልማት ድርጅት መካከል መስከረም ፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮድያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታህሳስ ፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው

## PROCLAMATION No.1069/2018

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CREDIT FACILITY AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE FRENCH DEVELOPMWENT AGENCY

**WHEREAS**, a Credit Facility Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the French Development Agency stipulating that the French Development Agency provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a credit facility in a maximum aggregate amount of 70,000,000 Euros (Seventy million EUR) for Financing the Relocation and Modernization of the Addis Ababa Abattorirs Enterprise Project, was signed in Addis Ababa on the 13th day of September, 2017;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀፅ ፶፭ (፩) (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ለአዲስ አበባ ቄራዎች ድርጅት ቦታ ማዛወሪያ እና ማዘመኛ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ ከፈረንሳይ የልማት ድርጅት የተገኘው ብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፷፱/፪ሺ፲"ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## ፪.<u>የስምምነት መፅደቅ</u>

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በፈረንሳይ ልማት ድርጅት መካከል መስከረም ፫ ቀን ፪ሺ፲ ዓም በአዲስ አበባ የተፈረመው የብድር ስምምነት ቁጥር CET 1058 01X በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፫.<u>የ ገ ንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስልጣን</u>

የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፸ ሚሊዮን ዩሮ (ሰባ ሚሊዮን ዩሮ) ብድር በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሰረት በስራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

## ፬.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከተወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር ፰ ቀን ፪ሺ፲ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

28th day of December, 2017; 1067

**NOW,THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## 1. <u>Short Title</u>

This Proclamation may be cited as the"French Development Agency Credit Facility Agreement for Financing the Relocation and Modernization of the Addis Ababa Abattoris Enterprise Project Ratification Proclamation No.1069/2018".

## 2. <u>Ratification of the Agreement</u>

The Credit Facility Agreement No.CET 1058 01X signed in Addis Ababa, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the French Development Agency on the 13th day of September, 2017 is hereby ratified.

## 3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utlilization of the credit amount of 70,000,000 Euros ( Seventy million million EUR) in accordance with the terms and conditions setforth in the Credit Facility Agreement.

## 4. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done of Addis Ababa, this 16th day of January, 2018**

**MULATU TESHOME (Dr.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ
ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

REPUBLIC OF ETHIOPIA